# አንበሳው አገሳ!!!

ተናግሬ ነበር ትዉልዱን አምቾ

ለግሉ የሚጣደፍ፣ በዕፅ የተበከለ፣ ለሞት የተመቸ

የማይቆረቆር፣ የማይቆጭ ወጣት፣ በስህተት አይቸ

ይቅርታ ጠየኩኝ፣ በጉልበቴ ቁሜ፣ በአፌ ተደፍቸ

ደፋርና ለጋስ ጀግና ዜጋ አግኝቸ

ኮራሁ በሃገሬ፣ ኮራሁ በወግገኔ፣ በእህት ወንድሞቸ

ወሸኔ!! ልበልሽ፣ አንበሳው!! ልበልህ ሌላ ቃል አጥቸ።

ጎንደር ከአፋፉ ላይ አንበሳው አገሳ

የልዩነት ደዌ ሊያጠፋ ነቀርሳ

በአንድነት ልሳኑ በመይሳው ካሳ

ሰንደቁን ከፍ አድርጎ፣ ዓላማውን ለብሶ፣ አገሩን ሊያነሳ

ጎንደር ከአፋፉ ላይ አንበሳው!! አገሳ።

ጎንደሬ ታሪኩ፣ ሃይማኖት...ባህሉ...ልማዱ  ምን ይላል

አያድርስ  ጠቡ...ቋያው ያቃጥላል

ጎራዴው ይቀላል....ጥይቱ ይቆላል

ትህትና.... ትዕግስቱ....ፍቅሩ ግን ይገድላል...ሰው በቁም ይጥላል

ጀግና ነው ጎንደሬ መከታ ይሆናል

ጨዋ ነው ጎንደሬ በዕዉነት ይታመናል።

ጎንደሬ ለጋስ ነው፣ ከፍቶ ይቀበላል....

አንጥፎ ያስተኛል ተርቦ የመጣን

ተዘክሮ የሚሸኝ ጠግቦ የተቆጣን

ውለታ የረሳ የተያዘ ቁንጣን

ትምክህተኛ እያለ በአድሎ የሚቀጣን።

ለሩብ ምዕት ዓመታት ሰመመን ዉስጥ ገብቶ

ቁሞ እያበራ፣ ተላብሶ እያበላ፣ ዉለታው ተረስቶ

ወጀዱ ሲታረስ...ልጆቹ ሲሸጡ..... ከቤቱ ሸፍቶ

አንበሳው አገሳ ስሜቱ ተናግቶ

አንበሳው አገሳ ደንበሩ ተነክቶ

አልሞ ሊመታ እራሱን ለይቶ

ጎንደሬ ተነሳ ሲግደረደር ሙቶ።

እሰይ የምስራች ችቦው ተለኮሰ

ታፍኖ ተቃጥሎ አየሩ እየጨሰ

ወልቃይት ተነስቶ አንገረብ ደረሰ

አክስጂን አግኝቶ ጎንደር ተነፈሰ

ስማ በለው  ብሎ እርችት ተኮሰ።

አረንጓዴ፣ ብጫ፣ ቀይ ባንዲራ ለብሶ

አንበሳው አገሳ አንገረብ ላይ ነግሶ።

ሽብርተኛ የሚባል ዘፈን ስለመጣ

ጎንደር ተሰልፎ አደባባይ ወጣ

ደግሞ እንደ ታች አምናው ዘንድሮም ተቆጣ

ትክክል የሚፈርድ ዳኛ ስለታጣ

አድሎ ባርነትን....ረሃብ ስደትን...ጉቦን....ግፍን የሚቀጣ።

ቤቱን አስለቅቀው፣ ባለቤቱን ደፍረው፣ ከሰፈሩ ሰፍረው

በክብር በአንድነት የመኖር ህግ ሰብረው፤

ሲገፉ ሲገፉ፣ ሲሞላ ሲደፉ

ሲበቅል ሲቀጥፉ፣ ሲያፈራ ሲያጠፉ፤

ፍቅርን በጥላቻ፣ ትዕግስትን በዛቻ

ሰደቡት፣ ፈተኑት፣ በእሳት አቃጠሉት ጎንደርን ለብቻ

በደሉት ገደሉት በአጋዚ ጡንቻ።

ሃይማኖቱን ንቀው.....በእግዚአብሔር ተሳልቀው

ትዕዛዙን  አፍርሰው  መንበር አስለቅቀው

አማራ ነህ ብለው ወገቡን አርቀው

መሃፀን አምክነው......ጥፋቱን አልቀው.... ፍራቱን አድንቀው

ሱሪውን አውልቀው..... ስጋውን ፋፍቀው.....አጥንቱን አድቅቀው።

ልጠዉት የማይደርቅ!! ነቅለዉት የሚፀድቅ!!.....ቆርጠዉት!! የማይወድቅ.

ሲተኙበት ፍራሽ....ሲለብሱት አንሶላ....ምቾት የሚጠብቅ

የማይነቃነቅ!!

የማይነጥፍ ጥገት ተገፍቶ የማያልቅ፤

ኢህአዴግ የጠላው፣ አላምጦ የበላው

ኢትዮጵያዊ.....አማራ.....ጎንደሬ ይኸ ነው

የነፃነት ድንጋይ መሠረት የጣለው።

ፈርቶ ነበረ... ደንግጬ ነበረ፣ ወላዶች መከኑ ሰው አለቀ ብየ

ለካስ ተኝቶ ነው ጎንደር የዘገየ

ስለቴን ላስገባ ጨለማው ሊወጣ ጭላንጭል ከታየ።

ሰሜን አርማጭሆ፣ ወልቃይት ጠገዴ፣ቋራና ጃኖራ፣ በእነ አጅሬ መንደር

ደምቢያና ፎገራ፣ ዉዶ አሞራ ገደል፣ ጋይንት ደብረታቦር

እብናት በለሳ፣ በእነ ስበር መንደር

ወያኔ አረገዘ ፣ ወንድ ወለደ ጎንደር

አደራ የሚሰጡት......ተው ተመለስ ብሎ.... የሚጠብቅ ደንበር።

አንበሳው ተነሳ ለ25 ዓመት ከተቀመጠበት

ትክል ድንጋይና የእናት ሞት ቁርቁሮት

የሱዳኑ ደንበር...የውልቃይ መሬት

የክልሉ  ክህነት.....አፋኝ ቡድን ድፍረት

የዋልድባው ገዳም.... የሸንኮራው ልማት

እየተነጠለ ....ዘሩ እየታጨደ... አማራ በጥይት

እየተቃጠለ በነፃነት ጥማት

ጎንደሬ ተነሳ....አንገዛም ብሎ በዘረኛ መንግሥት.....በከፋፋይ ስርዓት።

ጎንደር ከፋፉ ላይ አንበሳው አገሳ

ቆርጦ ለማስወገድ የጊዜን አንካሳ

ፍቆ ለማስለቀቅ የታሪክ ጠባሳ

ጎንደር ከአፋፉ ላይ አንበሳው አገሳ።

ኢትዮጵያ ከአፋፉ አንበሳው አገሳ

ደም የለመደ ጅብ የህሊና እሬሳ

በሰው ስጋ የሚኖር አሞራ ... ጥንብ አንሳ

ሰባብሮ ለመጣል አንበሳው አገሳ።

አድቅቆ ለመጣል ወይን ወንበዴውን

ወያላ.....ደላላ.. ጎሳ ነጋዴውን

ሹምባሽ! የባንዳ ልጅ አገር ነጋዴውን።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ!!!!

ጎንደር ይጠራሃል እንነሳ እያለ...ግፉ ያብቃ እያለ

ግራ ቀኝ ተላብሶ እያቀባበለ

የኢትዮጵያ ጠላት ክልል ዘረኝነት ይወገድ እያለ።

የትግራይ ህዝብ ሆይ!!!!

ተነሳ ለትግል....ወገንህን ምሰል....አገርህን ታደግ

በተንኮል ተወልዶ.....በትዕቢት አርጅቶ....

በግድ ይወገዳል.... ይወድቃል ኢህአዴግ።

ትግራይ ዘርን ትተህ በህሊና ፍረድ

አጥፊ ነው፣ ጠፊ ነው ወያኔ ኢትዮጵያን አትካድ።

ጠይቀው ተከዜን የት እንደሁ ደንበሩ

ስንቶች ገብተው ቀሩ?

ስንቶች ተሻገሩ? ምን ነበር ተግባሩ?

በሙላት፣ በጉድለት ዉሃው እያያቸው ሰዎች ሲታወሩ።

ትዉልድ በትዉልድ...መንግሥት በመንግሥት....ተተክቶ ያልፋል

እኛ እንዳገኘነው አገር ግን ይተርፋል

ታሪክ ክርክሩ....ታሪክ ፉክክሩ....ታሪክ ምስክሩ

ያነግሳል....ያረክሳል

ይከሳል...ይወቅሳል....

ይስቃል......ያለቅሳል

ይፅፋል...ይስላል...ዝማሬ ያፈሳል

ይፈርዳል.....ይቀዳል ቅኔውን ይዘርፋል።

እንደ አገር እንቀጥል፣ እንደ ህዝብ እንኑር

በእዉነት እንደሰት፣ አብረን እንቸገር።

እሪ በይ አድዋ ለአክሱም ተናገሪ

ምስክር ቁጠሪ ጥበብን ተማሪ

አብርሃ፣ አፅብሃ፣ አሉላ አባ ነጋ

ፋሲል፣ ቴዎድሮስን፣ ዮሐንስ፣ ምኒልክን ጥሪ

ደንበርሽን በአቃቅማ በእሾክ አትጠሪ

አንቺኑ እንዳይወጋሽ በጭፍን ስትመሪ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ!!!!

አለንህ እያሉ አስረው ያስቀመጡህ

የመንግሥት ጉልቶች ለንግድ የመረጡህ

ተጠንቅቀህ ተጓዝ.... ልክ እንደትናንቱ ዛሬም እንዳይሸጡህ።

ያደረጉት ሁሉ አልበቃ ብሏቸው

ዛሬም አላፈሩ...ዛሬም አላረፉ....ፀንተው ይገድላሉ፣ ነቀርሳዎች ናቸው

ታክመው አይድኑም ቆርጠን ካልጣልናቸው።

አንሻም ጥገና....አንሻም ሽንገላ....አንሻም ድለላ

ልቀቁ አገራችን ጉዳችሁ ሳይፈላ

ሰማዩ ሳይጨልም መሬቱ ሳይቀላ።

በምስራቅ በምዕራብ፣ በሰሜን በደቡብ፣ በከተማ ገጠር

አንድነት ሃይል ነው ክንድህን አጠንክር....ከፋፋዩን አባር።

መለዮ ለባሽ ሆይ!!

አባትክን...እናትክን....ወንድምክን...እህትክን...ሚስትህን...ልጅህን አትግደል

ከህዝብ ጋር ሁነህ...ጨቋኙን አስወግድ....የኢትዮጵያን ቀን አክብር

አብረን እንዘምር ቢሄራዊ መዝሙር

በክብር እናሰማ የህዝብ መፈክር "ህያው ድል በትግል"!!

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ!!!!

ነዉጠው፣ ቀዉጠው.....ወዝዉዘህ፣ ገልብጠው

ከፉን አንቀጥቅጠው.... ገመዱን ቁረጠው

ፍርዱን ዛሬ ስጠው።

ሆ!!! ብለህ “ተነሳ”.... አምርረህ “ተነሳ” ዛሬ ተነቃነቅ

ሙብት ነፃነትክን አገርህን ጠይቅ

ትግልህንም ምራ...ስልፍህን አስተካክል....ዓላማህን እወቅ

ለማንም አይበጅም ነገ ነገ እያሉ በየተራ መውደቅ

ክልሉን አፍርሰህ.....ጨዋነት ተላብሰህ.....ሰላምን አንግሰህ

አንተነትክን ጠብቅ!!!! አንድነትክን ጠብቅ!!!!።

አዲስ ምዕራፍ ጀምር.....ለትዉልድ የሚቀር

እግዚአብሔርን ፍራ.....አገርህን ዉደድ.....ወገንህን አክብር!!!!!!!

እንዲህ ነው ኢትዮጵያ!!!!እንዲህ ነው አማራ!!!!እንደዚህ ነው ጎንደር!!!!!

በማተቡ የሚዳኝ ዝናው የሚናገር

እስኪለብሳት ድረስ በጥርኝ አፈሩ የማይደራደር!!!!!!

እንዲህ ነው አንበሳው!!!!

እንዲህ ነው ኢትዮጵያ!!! እንዲህ ነው አማራ!!! እንደዚህ ነው ጎንደር!!!!!።

ኢትዮጵያ

በክብር፣ በነፃነት፣ በአንድነት፣ በሰላምና በፍቅር፣ ለዘላለም ትኑር!!!!

ኃይሉ

abirhanu@bellsouth.net